# ቅንጅት ያለበት ደርጃ ያሳሰባቸው አባላት
# የግንቦት 3 2000 ዓመተ ምህረት ስብሰባ ውጤት

የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ካለበት፡ አስከፊ፡ ሁኔታ፡ ይታደገኛል፡ ብሎ፡ በከፍተኛ፡ ደረጃ፡ የደገፈው፡ ቅንጅት፡ አሁን፡ ለሚገኝበት፡ ደርጃ፡ ለመድረስ፡ ያበቁት፡ ምክንያቶች፡ በሰፊው፡ ተመርምረዋል። እነዚህ፡ በእንግሊዝ፡ አገር፡ የሚኖሩ፡ የሃገርና፡ የወገን፡ ችግር፡ የተሰማቸው፡ ወገኖች፡ ችግሮቹን፡ አበጥረውና፡ አንጠርጥረው፡ ተወያይተዋል። እነዚህ የሃገርና የወገን ተቆርቋሪ የድጋፍ አባላት ቀደም ሲል ከመሠረቱት ዓቢይ ድርጅቶች ፡ ጋር በመሆን ፡ ጉልበታቸውን ፣ እውቀታቸውንና፣ ገነዘባቸውን፡ ሲያበረክቱ፡ የቆዩና፡ ቅንጅትም፡ሲፈጠር፡ የድጋፍ፡ ኮሚቴ፡ አባል፡ ሆነው፡ የላቀ፡ አስተዋጽኦ፡ ሲያደርጉ፡ የቆዩ፡ በመሆናቸው፡ ችግሮቹን፡ በነቂስ፡ መመርመር፡ ችለዋል። ካተኮሩበት፡ ጉዳዮች፡ አንዱ፡ እያንዳንዱ፡ ኢትዮጵያዊ፡ ር‧ብርቦሽ፡ አድርጎ፡ የተሰበሰበው፡ ገንዘብ፡ ለታለመለት፡ ዓላማ፡ የሚውልበትን፡ መንገድ፡ በሰፊው፡ ተውያይተዋል።

ሌላው፡ ትኩረት፡ ተሰጥቶ፡ አባላቱ፡ የተወያዩበት፡ ጉዳይ፡ የድጋፍ፡ አባላቱ፡ ይመሩኛል፡ ብሎ፡ ከመረጣቸው፡ አመራር፡ መካከል፡ አንዳንዶቹ፡ በጋራ፡ በመሥራት፡ ፋንታ፡ የግል፡ ቡድን፡ በመፍጥር፡ ቅንጅትን፡ ለስውር፡ ዓላማቸው፡ ለማዋል፡ አፍራሽ፡ ሚና፡ ሲጫወቱ፡ መቆየታቸው፡ በሰፊው፡ ተወስቶአል። በዚህ፡ በእንግሊዝ፡ ሀገር፡ ቅንጅት፡ ያለበት፡ ሁኔታ፡ ያሳሰባቸው፡ የድጋፍ፡ ድርጅቱ፡ አባላት፡ ስብሰባ፡ ግንቦት፡ 3ቀን፡ 2000ዓመተ፡ ምህረት፡(May 11/2008) ሲጠሩ፡ እነዚህ፡ መበተን፡ ሥራዬ፡ ብለው፡ የተያያዙት፡ ሰዎች፡ ቀደም፡ ሲል፡ የወጣውን፡ ጥሪ፡ በድረ፡ ገጽ፡ ከተመለከቱ፡ በኋላ፡ ሌላ፡ ስብሰባ፡ በዚሁ፡ ቀን፡ የጠሩበት፡ ያው፡ የተለመደውን፡ የመከፋፈል፡ ዓላማቸውን፡ ለመፈጸም፡ መሆኑን፡ ግንዛቤ፡ ተጨብጦበታል።

አፍራሹ፡ ቡድን፡ ቀድሞ፡ ያልነበሩ፡ ስለተፈጠረው፡ ችግር፡ በቂ፡ ግንዛቤ፡ የሌላቸውን፡ አዳዲስ፡ ሰዎችን፡ አሰባስቦ፡ የራሱ፡ የአገልግሎት፡ ግዜ፡ ገደብ፡ አልቆ፡ ስላገለላችውም፡ ሆነ፡ ስላሉት፡ ችግሮች፡ ሳያነሳ፡ ያው፡ የተለመደ፡ የቡድን፡ ሥራውን፡ ፈጽሟል።

ሀቁን፡ የሚያውቁ፡ ሰዎች፡ ባልተገኙበት፡ እውነቱን፡ ሸሽጎ፡ ድርጅቱን፡ ለመቆጣጠር፡ መሯሯጡን፡ የተያያዘውን፡ የዚህን፡ ችግር፡ አካል፡ መታረም፡ እንደሚያስፈልገው፡ ስብሰባው፡ አበክሮ፡ ገልጿል። ለቅንጅት፡ የተሰበሰበውን፡ ገንዘብ፡ አፈንጋጩ፡ ሊቆጣጠር፡ ቢሞክርም፡ ከህግና፡ ከደንብ፡ አኳያ፡ ከተጠያቂነት፡ እንደማይድን፡ ሊያውቀው፡ ይገባል፡ ሲል፡ ተሰብሳቢው፡ ውሳኔ፡ ሲያሳልፍ፡ ገንዘቡ፡ ለቅንጅት፡ የሚሆንበትን፡ መፍትሄዎች፡ በመሰንዘር፡ ድምዳሜ፡ አሳብ፡ ላይ፡ደርሷል።

በማያያዝም፡ የአገራችን፡ በጣም፡ አሳሳቢና፡ የከፋ፡ ሁኔታ፡ በቀላሉ፡ የማይገመት፡ መሆኑ፡ በሰፊው፡ ተወስቷል። በተለይም፡ ለህሊና፡ የሚዘገንና፡ ማንኛውም፡ ዜጋ፡ ሊቀበለው፡ የማይችለው፡

ጉዳይ፡ በተለያዩ፡ የዜና፡ አውታሮች፡ እንደተጠቀሰው፡ የራስችን፡ መንግሥት፡ ከጎንደር፡ እስከ፡ ጋምቤላ፡ ያለውን፡ ረጅም፡ የሱዳን፡ አዋሳኝ፡ መሬት፡ በርካታ፡ ኪሎሜትር፡ ወደ፡ ውስጥ፡ ዘልቆ፡ ለሱዳን፡ መስጠት፡ ነው። ይህ፡ መንግሥት፡ ሃገሪቱን፡ እየቆራረሰ፡ ሉአላዊነቱን፡ እየደፈረ፡ ስለሆነ፡ ተገቢውን፡ ርብርቦሽ፡ በማድረግ፡ ድርጊቱ፡ እንዲከሽፍ፡ ማድረግ፡ የወቅቱ፡ አንገብጋቢ፡ ሥራ፡ እንደሆነ፡ በሰፊው፡ ተነጋግሮበታል። በሌላ፡ በኩል፡ በሃገሪቱ፡ ረጅም፡ ታሪክ፡ በሌላ፡ ሀገር፡ ጉዳይ፡ ጣልቃ፡ ገብታ፡ የማታውቀውን፡ ሀገርችንን፡ በሰላም፡ ማስከበር፡ ስም፡ ወታደራዊ፡ ኃይል፡ ልኮ፡ ባንዳንድ፡ የዜና፡ አውታሮች፡ እንደተዘገበው፡ ተፈጸሙ፡ የሚባሉትን፡ ጉዳዮች፡ ተወያይቶበታል። በዚሁም፡ ምክንያት፡ ለውደፊት፡ ሊያስከትል፡ የሚችለውን፡ መዘዝም፡ ግንዛቤ፡ ተጨብጠበታል።

በምእራቡ፡ የሃገራችን፡ ክፍል፡ የተሰጠውን፡ መሬት፡ ጉዳይ፡ የሚመረምርና፡ የችግሩን፡ ስፋትና፡ጥልቀት፡ የሚያጠና፡ ለችግሩ፡ መፍትሄ፡ የሚሻ፡ አስተባባሪ፡ ኮሚቴ፡ መርጧል። በሀገር፡ ቀልድ፡ የለም፡ ነውና፡ እያንዳንዱ፡ ኢትዮጵያዊ፡ ተሳትፎበት፡ ጉዳዩን፡ ከእልባት፡ ማድረስ፡ እንደሚጠበቅበትና፡ አስፈላጊውን፡ ሁሉ፡ ማድረግ፡ እንደሚያሻ፡ ተሰብሳቢው፡ በሙል፡ አጽንኦት፡ ውሳኔ፡ አሳልፏል።

**የኢትዮጵያ ሕዝብ የውሸተኞች መቀለጃ አይሆንም!!!**
**ኢትዮጵያ በተንኮለኞች ደባ አትቆራረስም!!!**
**ኢትዮጵያና ሕዝቧን ከበግ ለምድ ለባሽ ቀበሮዎች አምላክ ይጠብቅልን!!!**